# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 25 ኛ ሳምንት
## ኒቆዲሞስ

**ዓላማ**

- *መንፈሳዊ ትምህርት የመፈለግን ጥቅምና ስለጥምቀት አስፈላጊነት መማር*

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።"*** ዮሐ.3÷5

**ምንባብ**

- ዮሐ. 3÷1-15

**መግቢያ**

- *ፈሪሳውያን* ሕግን በመጠበቅ ተጠያቂዎች ነን ብለው የሚያምኑ የአይሁድ ምሁራን ነበሩ።
- ኒቆዲሞስም ከእነዚህ አንዱና፤የተማረ የፈሪሳውያን አለቃም ነበር። በዛሬው ትምህርታችን ኒቆዲሞስ ለመንፈሳዊ ትምህርት ከነበረው ጉጉት አንጻር የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር - ***ምሥጢረ ጥመቀትን*** እንዴት እንደተማረ እንማራለን።

**ትምህርቱ**

- ከክርስቶስ ለመማር የሚመጣ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው ነበር።በጣም የተማረ ቢሆንም ከጌታችን መማር እንዳለበት አምኖ ይመጣ ነበር፤የአይሁድ ሊቅና ከፈሪሳውያን ወገን ስለነበረም ማንም እንዳያየው በሌሊት ወደ ጌታችን መጥቶ ይማራል።
- አንድ ሌሊትም ጌታችን ስለጥምቀት አስተማረው።
- አንድ ቀን ኒቆዲሞስ በሌሊት መጥቶ ***"መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዳመጣህ እናውቃለን።"*** አለው።
- ጌታችንም ***"እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት አያይም"*** አለው።
- ኒቆዲሞስም ተደንቆ***"ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?"*** አለ።
- ጌታችንም***"ዳግመኛ መወለድ"*** ምን ማለት እንደሆነ አብራራለት።***"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም።ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው÷ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።"*** አለው።

**በዚህ ትምህርት መሠረትም ፡-**

- ቤተክርስቲያን ልጆችንና አዲስ አማኝያንን ከውሃና ከመንፈስ ዳግመኛ ታጠምቃለች።
- እናት ልጇን ታቅፋ ስትቀመጥ፤ካህናትና ዲያቆኑ ቆመው በማጥመቂያ ዙሪያ ይጸልያሉ።የክርስትና አባትናእናትም ጸሎተ ሃይማኖት ደግመው ስለ እግዚአብሔር ሊያስተምሩ ቃል ይገባሉ።ካህኑም የክርስትና ስም ይሠጣሉ። ***የክርስትና ስም ምንድነው?*** ተወያዩበት።
- ተጠማቂው ሕጻን ከተጠመቀ/ች/በኋላ፤ሜሮን ይቀባሉ፤መንፈስ ቅዱስም ያድርባቸዋል፤ከውሃና ከመንፈስ መወለድ ማለትም ይህ ነው፤
- ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክስቶስ ለኒቆዲሞስ እንዳስተማረውም ያልተጠመቀ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም።
- አዲስ ምሥጢር እንደ ኒቆዲሞስ እንዲገልጥልንም፤ከእግዚአብሔር ለመማር ያለን ፍላጎት ሁሌም በጉጉት መሆን አለበት።
- ኒቆዲሞስ ምሁር እንኳን ሆኖ ሳይኮራና ይበቃኛል ሳይል ይማር ነበር።በዚህም ስለ ሰማያዊ ምሥጢርን ተማረ።
- ከሥርዓተ ጥምቀት ፍጻሜ እስኪ.ቆርቡም ሕጻኑ/ኗ/ ይጾማሉ።ከዚያም ይቆርባሉ።

**ምን እንማራለን**

1. **የጥምቀት ጥቅም** ጥምቀት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የሚያስፈልገንና የምንፈጸመው ምሥጢር ነው፤ጌታችን ለኒቆዲሞስ ያስተማረውና በእርገቱ ለደቀመዛሙርቱ ያዘዛቸውም ይሄንኑ ነው።***"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው።"*** ማቴ. 28÷19
2. **የመማር ፍላጎት**
   - ከኒቆዲሞስ ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ትምህርት የመፈለግን ጥቅም እንማራለን።ኒቆዲሞስ ለመማር ለመጠየቅ በነበረው ጉጉት ምሥጢር እንደተገለጠለት እግዚአብሔር ለእኛም ይገልጥልናል።
   - በተጨማሪም የመማር ፍላጎታችን ሌላ እውቀት ስላለን መቆም የለበትም ኒቆዲሞስ ምሁር ሆኖም ሊማር በሌሊት ይገሠግስ ነበርና፤የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ምሥጢርን ተረዳ።

**ማጠቃለያ**

- 7ኛው የአቢይ ጾም ሳምንት ኒቆዲሞስ ይባላል።ስለ ጥምቀት መንፈሳዊ ምሥጢር ይተነተንበታል።
- አንድ ሰው ሲጠመቅ ሦስት ምሥጢራት ይፈጽሙላታል፡- ምሲጠረ ጥምቀት፣ ሜሮንና ቁርባን።

**ጥያቄዎች**

1. ኒቆዲሞስ ከየትኛው የአይሁድ ክፍል ይቆጠራል? ለምን ከክርስቶስ ለመማር ፈለገ?
2. ዳግመኛ መወለድ ምን ማለት ነው? የጥምቀት ጥቅም ምንድን ነው?
3. ጌታችን ሲያርግ ለደቀመዛሙርቱ ያዘዘው ትዕዛዝ ምንድነው? ስለ እግዚብሔር መማር ጥቅሙ ምንድ ነው?
4. 7ኛው የዐቢይ ጾም ሳምንት ስለ ምን የምንማርበት ነው? ለምንስ ይታሰባል?

**ይቆየን።**